# በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱና እንዲያንቀሳቅሱ ለመፍቀድ የወጣውን መመሪያ ቁጥር ኤፍ.ኤክስ.ዲ/25/2004 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር ኤፍ.ኤክስ.ዲ/31/2006

በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱ መፍቀድ የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ ሆኖ በመገኘቱ፣

በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲያንቀሳቅሱ ማድረግ የአገሪቱን የአለም አቀፍ መጠባበቂያ ሂሳብ የሚደግፍ በመሆኑና የአገሪቱን የክፍያ ሚዛን ችግር ሊያቃልል እንደሚችል በመታመኑ፣

በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱ መፍቀድ ለውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰት አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ በመጠበቁ፤

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በገንዘብና ባንክ አዋጅ ቁጥር 83/1994 አንቀጽ 6 እና 61 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ በአገር ውስጥ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የሚከፍቱበትን ሁኔታ በሚመለከት የወጣውን መመሪያ ቁጥር ኤፍ.ኤክስ.ዲ/31/2004 ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## አንቀጽ - 1
## ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር ድረስ በዚህ መመሪያ:-

1.1 "በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን" ማለት

ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸውና በውጭ አገር ከአንድ አመት በላይ የኖሩና እየሠሩ የሚገኙ ግለሰቦች፣

ለ) በውጭ አገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ባለቤትነት የሚካሄዱና ከአንድ አመት በላይ በውጭ አገር በሥራ ላይ ያሉ የንግድ ድርጅቶች፣

ሐ) በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወይም ከአንድ ዓመት በላይ ለሚያቆይ ሥራ ወደ ውጭ አገር ለመሄድ በዝግጅት ላይ ያሉና አስፈላጊውን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ማለት ነው::

1.2 "በውጭ አገር የሚኖሩ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች" ማለት

ሀ) በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነና ይህንኑ ተወላጅነቱን በአዋጅ ቁጥር 270/94 መሠረት የሚገልጽ መታወቂያ የሚያቀርብ በውጭ አገር ነዋሪ የሆነ ግለሰብ፣

ለ) በውጭ አገር በሚኖሩና በትውልድ ኢትዮጵያዊ በሆኑ የውጭ አገር ዜጎች ባለቤትነት በውጭ አገር በሥራ ላይ ያሉ የንግድ ድርጅቶች ማለት ነው::

1.3 "በውጭ አገር የሚኖሩ ግለሰቦች/ድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ" ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ላይ የተገለፁትን በውጭ ምንዛሪ የሚከፈቱትንና ያለባንኩ ፈቃድ በአገር ውስጥ በጥቅም ላይ ሊውሉ ወይንም ወደ ውጭ ሊላኩ የሚችሉትን ሁለቱን ሂሳቦች ማለት ነው::

1.4 "ሂሳብ የሚከፍቱ ባንኮች" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ ፈቃድ የተሰጣቸው ንግድ ባንኮች ናቸው::

1.5 "ባንኩ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው::

1.6 "ሂሳብ" ማለት በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች በውጭ ምንዛሪ የሚከፍቱትን ሂሳብ ነው::

1.7 "ሰርተፊኬት" ማለት አስቀማጮች ላስቀመጡት ገንዘብ በንግድ ባንኮች የሚሰጥ የተቀማጭ ገንዘብ ባለቤትነት የሰነድ ማስረጃ ነው::

1.8 "የውጭ ምንዛሪ ገንዘቦች" ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ላይ የተዘረዘሩትና በባንኩ ተቀባይነት ያላቸው አራቱ የውጭ ምንዛሪ ገንዘቦች ናቸው::

1.9 "ተቀማጭ" ማለት ሂሳብ ከፋቹ ባንክ በውጭ ምንዛሪ ከባለመብቱ የተቀበለው የገንዘብ ተቀማጭ ሲሆን ይህም የጥሬ ገንዘብ ሰርተፊኬት፣ ቼክ እና ሌሎች ተመሳሳይ የተቀማጭ አይነቶችን ይጨምራል፡፡

## አንቀጽ 2
## የብቁነት መስፈርቶች

2.1 ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ፈቃድ በተሰጣቸው ንግድ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱ ተፈቅዶላቸዋል፡፡

እነርሱም፡-

ሀ) በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ እና

ለ) በውጭ አገር የሚኖሩ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች ናቸው፡፡

2.2 በአገር ውስጥ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ለመክፈት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች ቀጥሎ የተመለከቱትን መረጃዎች (ሰነዶች) ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

እነርሱም፡-

ሀ) በትክክል የተሞላና በሂሳብ ከፋቹ የተፈረመበት የማመልከቻ ቅጽ (ፎርም)፣

ለ) ለግለሰብ አመልካቾች፤ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የኢትዮጵያዊነት ፓስፖርት፣ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች ደግሞ ዜግነት የወሰዱበትን አገር መታወቂያ፣ እና

ሐ) ለድርጅት አመልካቾች የድርጅት ባለቤትነት ማስረጃና የድርጅት መመሥረቻ ሰነድ (memorandum of association) ናቸው፡፡

2.3 በአገር ውስጥ ባንኮች በአካል ተገኝተው ሂሳብ መክፈት የማይችሉ አመልካቾች በአቅራቢያቸው የሚገኙ የኢትዮጵያ ኢምባሲ፣ ከኢትዮጵያ ባንኮች ጋር የሂሣብ ግንኙነት ያላቸው /ኮርስፖንዳንት/ ባንኮች ወይም የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶችን በመጠቀም መክፈት ይችላሉ፡፡

# አንቀጽ 3
## የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ መክፈት

3.1 በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2.1 የተጠቀሰውን የብቁነት መስፈርት ላሟሉ ግለሰቦች እና/ወይም ድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ሊከፈትላቸው ይችላል፡፡

3.2 ሂሳቡን ለመክፈት መብት የተሰጣቸው በውጭ የሚኖሩ ግለሰቦች በአካል በመቅረብ ወይም በፖስታ ሂሳብ መክፈት ይችላሉ፡፡ ሂሳብ የሚከፍቱ ባንኮችም ኢ-ሜይል፣ ፋክስ፣ ቴሌክስ ወይም ባንኩ የሚፈቅዳቸውን ሌሎች አስተማማኝ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ከሂሳብ ከፋቾች ጋር ግንኙነት መፍጠር ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ሂሳቡን ለመክፈት ከፋቹ ባንክ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች መቀበል ይኖርበታል፡፡

3.3 የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ለመክፈት ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው የማመልከቻ ደብዳቤና የፊርማ ማረጋገጫ ሰነድ (specimen signature) አያይዞ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

3.4 ማንኛውም ግለሰብ እና/ወይም ድርጅት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4.1 የተዘረዘሩትን ሁሉንም ወይንም አንዱን አይነት የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ለመክፈት ይችላል፡፡

3.5 ሕጋዊ ወኪሎች በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን እና/ወይም በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎችን በመወከል የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ወደ ሂሳቦቹ እንዲያስገቡ አይፈቀድም፡፡ ነገር ግን ወኪሉ ከውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ወጪ እያደረገ አንቀፅ 7.1 ላይ ለተዘረዘሩት ተግባራት እንዲያውል የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ባለቤት በሕጋዊ መንገድ በግልጽ የወከለው ከሆነ ከዚሁ ሂሳብ በአገር ውስጥ ገንዘብ ወጪ ለማድረግ ይፈቀድለታል፡፡

3.6 የተንቀሳቃሽ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ለመክፈት አነስተኛው የመነሻ ተቀማጭ 100 (አንድ መቶ) የአሜሪካን ዶላር ወይም ከዚሁ ጋር ተመጣጣኝ የሆነና በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 5.1 በተመለከቱት የተፈቀዱ የውጭ ምንዛሪ ገንዘቦች የቀረበ ተቀማጭ ነው፡፡

3.7 የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳብ ለመክፈት አነስተኛው የመነሻ ተቀማጭ 5000 (አምስት ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ወይም ከዚህ ጋር ተመጣጣኝ የሆነና በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 5.1 በተመለከቱት የተፈቀዱ የውጭ ምንዛሪ ገንዘቦች የቀረበ ተቀማጭ ነው፡፡

3.8 የተንቀሳቃሽ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ጣሪያ 50,000 (ሃምሳ ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ነው::

3.9 የብቁነት መስፈርቱን የሚያሟሉ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ አስቀማጮች በመቀናጀት አንድ የጋራ ሂሳብ መክፈት ይችላሉ::

3.10 አንድ ግለሰብ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ መክፈት የሚችለው በአገር ውስጥ ከሚገኙት ባንኮች በአንዱ ብቻ ሲሆን የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳብ ግን በተለያዩ ባንኮች ውስጥ መክፈት ይችላል::

## አንቀጽ - 4
## የተፈቀዱ ሂሳብ አይነቶች

4.1 ንግድ ባንኮች ቀጥሎ የተመለከቱትን በውጭ አገር የሚኖሩ ግለሰቦች/ድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ሊከፍቱ ይችላሉ::

ሀ) አንደኛው የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳብ ሲሆን፣ ይህም በአስቀማጩ ስም በሚዘጋጅ የተቀማጭ ሰርተፊኬት (deposit certificate) አማካኝነት የሚከናወን ነው:: የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ለክፍያ የሚደርስበት ጊዜ (maturity period) በአስቀማጩና በሂሳብ ከፋቹ ባንክ መካከል በሚደረግ ስምምነት የሚወሰን ሲሆን፣ ሂሳቦች ለክፍያ የሚደርሱበት የጊዜ ገደብ ከ3 ወር ማነስ የለበትም::

ለ) ሁለተኛው የተንቀሳቃሽ ሂሳብ ሲሆን፣ ይህም በማንኛውም ጊዜ ወጪ ለማድረግ ቼክ በማዘጋጀት ወይንም ሂሳብ ከፋቹ ባንክ በሚያዘጋጀው የተለየ ስርዓት (pre-arranged procedure) ገንዘብ ወጪ የሚደረግበት ነው::

ሐ) ሦስተኛው ወደ ውጭ ሊወጣ የማይችል የብር ሂሣብ /Non-repatriable Birr Account/ ሲሆን ይህም በቁጠባ ሂሳብ መልክ ሆኖ በአገር ውስጥ ለሚደረጉ ወጪዎች ብቻ የሚውል ይሆናል::

## አንቀጽ - 5
## የውጭ ምንዛሪ ገንዘብ አይነቶች

5.1 የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች የሚከፈቱት ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ገንዘቦች ብቻ ይሆናል::

እነርሱም:-

ሀ) የአሜሪካን ዶላር፣

ለ) የእንግሊዝ ፓውንድ፣

ሐ) ዩሮ፣ ናቸው::

## አንቀጽ - 6

## ገንዘብ ወደ ውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የሚገባበት ሥርዓት

6.1 ውጭ አገር በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና በትውልድ ኢትዮጰያዊ በሆኑ የውጭ አገር ዜጎች የተከፈቱ የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች ቀጥሎ በተመለከቱት በአንዱ ወይንም በሁለቱ የገንዘብ ማስተላለፊያ መንገዶች ከውጭ አገር በመነጨ ገንዘብ ብቻ ገቢ መደረግ አለባቸው::

ሀ) ከውጭ አገር በቀጥታ በባንክ በኩል የሚደረግ ሀዋላ(direct crediting)፣

ለ) የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ያለው ግለሰብ ከውጭ ይዞት የሚገባው የመንገደኞች ቼክ፣

ሐ) የውጭ ምንዛሪ በጥሬ ገንዘብ ይዞ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ግለሰብ በገባበት ወቅት ለጉምሩክ ያሳወቀበት (declare) ያደረገበት ማስረጃ ሲያቀርብ፣

መ) ከውጭ አገር የመነጩ ልዩ ልዩ ቼኮች፣ እና

ሠ) ከሌሎች የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች የሚተላለፍ ገንዘብ (transfer)::

ረ) በዓለም አቀፍ የክፍያ ካርዶች የሚደረጉ ክፍያዎች::

## አንቀጽ - 7

## በውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የተቀመጠ ገንዘብ አጠቃቀም

7.1 በውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የተቀመጠን ገንዘብ ቀጥሎ ለተመለከቱት ተግባራት ለማዋል ይቻላል:: ይኸውም:-

ሀ) በአገር ውስጥ በብር ለሚፈጸሙ ክፍያዎች፣

ለ) ወደ ሌሎች የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች ለማስተላለፍ፣

ሐ) ለገቢ ንግድና ለሌሎች የውጭ የአገልግሎት ክፍያዎች (foreign service payments)፣

መ) ወደ ውጭ አገር ለማስተላለፍ፣

ሠ) በገበያ ላይ ባለው የምንዛሪ ምጣኔ መሠረት ወደ ብር ሂሳብ ለመለወጥ፣

ረ) የባንክ አገልግሎት ክፍያን ለመፈጸም እና

ሰ) ለብድር ወይም ለጨረታ እንደ ዋስትና ወይም መያዣ ለማገልገል ይውላል::

7.2 የተንቀሳቃሽ ሂሳብን ቼክ በመፃፍ እና የገንዘብ ማውጫ ፎርም (ቅጽ) በመሙላት ወይንም በሌላ በቅድሚያ በተዘጋጀ ሥርዐት ወጪ ማድረግ ይቻላል::

7.3 የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ባለቤት በአንቀጽ 4 ላይ በተለገፁት የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች ውስጥ ያለውን ተቀማጭ መልሶ ወደ ውጭ አገር ለመውሰድ ጥያቄ ካቀረበ ሂሳብ ከፋቹ ባንክ መፍቀድ አለበት::

7.4 ወደ ውጭ ተመልሶ የሚሄደው ተቀማጭ ከመነሻ ተቀማጩና ከተገኘው የወለድ መጠን መብለጥ የለበትም::

## አንቀጽ - 8

## የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የሚዘጋበት ሁኔታ

8.1 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ላይ የተመለከተውን የጊዜ ገደብ ተቀማጭ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ አስቀማጩ ከ7 የሥራ ቀናት ያላነሰ የቅድሚያ ማስታወቂያ (notification) በመስጠት ሲጠይቅ ሊዘጋ ይችላል:: በጊዜ ገደብ የተቀመጠን ተቀማጭ ጊዜው ሳይደርስ ወጪ ማድረግ የወለድ ቅጣት ያስከትላል::

8.2 አንድ የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ገንዘብ የጊዜ ገደቡ ሲደርስ ካልተዘጋ ሂሳብ ከፋቹ ባንክ ገንዘብ አስቀማጩን በማማከር ለተመሳሳይ የተቀማጭ ጊዜ ሊያድሰው ይችላል::

8.3 የጊዜ ገደብ ተቀማጭን የተቀማጭ ሰርተፊኬትንና በባንክ የተቀመጠን የፊርማ ሰነድ በማቅረብ ወይም በሌላ በቅድሚያ በተዘጋጀ ስርአት (pre-arranged procedure) ወጪ ማድረግ ይቻላል::

8.4 ሂሳቡን ለመክፈት የዋለው ገንዘብ በህገወጥ መንገድ የገባ ወይም የአሸባሪነት እንቅስቃሴን ለመርዳት የገባ ሆኖ ከተገኘ ሂሳቡ ይዘጋል::

## አንቀጽ - 9

## የወለድ ተመን

9.1 በውጭ አገር የሚኖሩ ግለሰቦች/ድርጅቶች ተንቀሳቃሽ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ወለድ አይከፈልበትም::

9.2 የንግድ ባንኮች በውጭ አገር የሚኖሩ ግለሰቦች/ ድርጅቶች በሚከፍቷቸው የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳቦች ላይ የሚከፍሉትን ወለድ በራሳቸው መወሰን ይችላሉ:: ነገር ግን የወለድ ተመኑ በጊዜው ካለው

በለንደን በባንኮች መካከል በሚደረግ ግብይት ከሚወሰን የወለድ ተመን (LIBOR rate) መብለጥ የለበትም፡፡

9.3 በውጭ አገር የሚኖሩ ግለሰቦች/ድርጅቶች የጊዜ ገደብ ተቀማጭ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ወለድ የሚከፈለው ቢያንስ ለ3 ወራት በባንክ ውስጥ ከተቀመጠ ብቻ ነው፡፡

9.4 በቅዳሜ፣ እሁድ፣ በበአል ቀን፣ እና በሌሎች የሥራ ቀናት ባልሆኑ ላይ ለክፍያ ብቁ (mature) በሚሆን የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳብ ላይ የሚከፈለው የወለድ ተመን የሚወሰነው በተከታዩ የሥራ ቀን ባለው ሁኔታ መሠረት ይሆናል፡፡

9.5 ወደ ውጭ በማይወጣ የብር ሂሳብ ላይ የሚከፈለው የወለድ ተመን ባንኩ የሚያስቀምጠውን ዝቅተኛው የተቀማጭ የወለድ ተመን እጥፍ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ - 10
## የተቀማጭ ሰርቲፊኬት አሰጣጥ

10.1 የሚከፈተው ሂሳብ የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳብ ከሆነ ሂሳብ ከፋቹ ባንክ ለአስቀማጩ በስሙ የተዘጋጀ የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሰርቲፊኬት (fixed deposit certificate) መስጠት አለበት፡፡

10.2 ከፋቹ ባንክ ለመክፈል የተስማማው የወለድ ተመን በሰርተፊኬቱ ላይ በግልፅ መቀመጥ አለበት፡፡

10.3 የሚከፈተው ሂሳብ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ከሆነ ሂሳብ ከፋቹ ባንክ ለአስቀማጩ የቼክ ደብተር ወይንም ሂሳብ መከፈቱን የሚገልጽ የባንክ መግለጫ (advice) መስጠት አለበት፡፡

10.4 ሂሳቡ የተከፈተው በንዑስ አንቀጽ 3.2 በተገለፀው ሁኔታ ከሆነ የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሰርቲፊኬት ወይንም የቼክ ደብተር በሂሳብ ከፋቹ ባንክ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ሂሳብ ከፋቹ ባንክ የተቀማጭ ሰርቲፊኬቱን ወይንም የቼክ ደብተሩን ማስቀመጡን የሚገልጽ ሰርቲፊኬት (certificate of custody) ለአስቀማጩ መስጠት አለበት፡፡ አስቀማጩ ግለሰብ ወይም ድርጅት የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሰርቲፊኬቱ እንዲሰጠው ከጠየቀ በፖስታ ሊላክለት ይችላል፡፡

## አንቀጽ - 11
## የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ወደ ብር ሂሳብ ስለሚቀየርበት ሁኔታ

11.1 በውጭ የሚኖር የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ባለቤት የመኖሪያ አድራሻ ከውጭ አገር ወደ አገር ቤት በሚቀየርበት ጊዜ በስሙ/በስምዋ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ በወቅቱ በሚኖረው የብር የውጭ ምንዛሪ ተመን ተሰልቶ ወደ ብር ሂሳብ ይዛወራል፡፡

11.2 ምንም እንኳን የሂሳቡ ባለቤት የመኖሪያ አድራሻ ከውጭ ወደ አገር ቤት ቢቀየርም በጊዜ ገደብ የተቀመጠ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የጊዜ ገደቡ እስከሚደርስ ድረስ በነበረበት ይቀጥላል፡፡ ነገር ግን የጊዜ ገደቡ እንዳለቀ የውጭ ምንዛሪ ሂሣቡ ወደ ብር ሂሳብ ይቀየራል፡፡

11.3 የሂሳቡ ባለቤት ከጠየቀ በአንቀጽ 7.1(ሠ) የተጠቀሰው ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ - 12
## የተከለከሉ ጉዳዮች

12.1 ከውጭ ምንዛሪ ቢሮዎችም ሆነ ከሌሎች የሀገር ውስጥ የውጭ ምንዛሪ ምንጮች የተገዛን የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች ለመክፈት ወይም ወደ እነዚህ ሂሳቦች ገቢ እንዲደረግ መጠቀም አይቻልም፡፡

12.2 የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ባላቸው ግለሰቦች ተጽፈው የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱ ላልተፈቀደላቸው ግለሰቦች ተከፋይ እንዲሆኑ የሚያዙ ቼኮች ተከፋይ የሚሆኑት በብር ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ - 13
## የንግድ ባንኮች ግዴታ

13.1 የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የሚከፍት ማንኛውም ንግድ ባንክ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፣

ሀ) የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ባለቤትን ሚስጥር መጠበቅ፡፡

ለ) ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ፎርም መሠረት የተከፈቱ ሂሳቦችን የሚያሳይ ሪፖርት በየወሩ ወሩ በገባ እስከ ሃያ ቀን ድረስ ለባንክና

የውጭ ምንዛሪ ዳይሬክቶሬት እንዲሁም ለኢኮኖሚ ጥናትና ሞነተሪ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት መላክ ይኖርበታል።

ሐ) በመመሪያ ቀጥር SBB/23/97 መሠረት በእያንዳንዱ የሥራ ቀን መጨረሻ ላይ በንግድ ባንኮች የሚገኘው ያልተሸፈነ የውጭ ምንዛሪ ሁኔታ (overall open foreign currency position) ከባንኩ ጠቅላላ ካፒታል 15 በመቶ መብለጥ የለበትም።

## አንቀጽ - 14
## ማበረታቻዎችን ስለመስጠት

14.1 በሂሳቡ ውስጥ የሚገኘው ገንዘብ በብር ከአገር ውስጥ ባንኮች ለሚወሰዱ ብድሮች የከፋቹን ባንክ የብድር ፖሊሲ ባገናዘበ መልኩ እንደ ዋስትና ሊያገለግል ይችላል።

14.2 በውጭ የሚኖሩ ግለሰቦች/ ድርጅቶች ከሚከፍቱት የጊዜ ገደብ ተቀማጭ የሚገኘው ወለድ ከገቢ ግብር ነፃ ነው።

14.3 ከነዚህ ማበረታቻዎች በተጨማሪ ባንኮች ለሂሳብ ከፋቾች የሚከተሉትን አመቺ ሁኔታዎች ይፈጥራሉ።

14.3.1 ባንኮች የሂሳቡን ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት በየወሩ ለሂሳቡ ባለቤት ይልካሉ።

14.3.2 ባንኮች ምስጢራዊ ቃል መፍቻ (test key) በመፍጠር የሂሳቡ ባለቤት ከሂሳቡ ወጪ እንዲያደርግና የአገር ውስጥ ክፍያዎችን እንዲፈፅም ያደርጋሉ።

14.3.3 ባንኮች ከሂሳቡ የተገኘውን ወለድ ወደ ሂሳቡ ቢያንስ በየሦስት ወሩ ያስገባሉ።

14.3.4 ባንኮች የሂሳቡ ባለቤት ቋሚ ወጪዎችን ለማድረግ የሚያስችለውን ሁኔታ ይፈጥራሉ።

14.3.5 ባንኮች እነዚህን ሂሳቦች ለመክፈት የሚያግዟቸውን በውጭ የሚገኙ የኮረስፖንዳንት ባንኮችንና ሌሎች ወኪሎችን በግልፅ ዘርዝረው ማሳየት አለባቸው።

## አንቀጽ - 15
## ምርመራ

እያንዳንዱ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የሚከፍት ንግድ ባንክ በዚህ መመሪያ መሠረት መሥራቱን ለማረጋገጥ ባንኩ በማንኛውም ጊዜ ምርመራ ሊያደርግ ይችላል::

## አንቀጽ - 16
## ቅጣት

16.1 ማንኛውም የዚህን መመሪያ አንቀጽ የጣሰ ንግድ ባንክ የባንክን ሥራ ስለመፍቀድና ስለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር SBB/27/2001 መሠረት ተጠያቂ ይሆናል::

16.2 በአንቀፅ 13.1 (ለ) ላይ የተመለከተውን ሪፖርት የመላኪያ ጊዜ ያዘገየ ማንኛውም ባንክ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ብር 1,000 (አንድ ሺህ) ቅጣት ይጣልበታል:: ይህም ቅጣት ወዲያውኑ ብሔራዊ ባንክ ከሚገኘ ው የባንኩ ሂሳብ ተቀናሽ ተደርጐ ገቢ ይሆናል::

16.3 ማንኛውም የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ባለቤት ይህንን መመሪያ መጣሱ እንደተረጋገጠ ሂሳቡን የከፈተው ንግድ ባንክ ሂሳቡን ለጊዜው በማገድ ጉዳዩን በአፋጣኝ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ ይኖርበታል::

## አንቀጽ - 17
## የተሻሩ ህጐች

በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ አገር ዜጐች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱና እንዲያንቀሳቅሱ ለመፍቀድ የወጣው መመሪያ ቁጥር ኤፍ.ኤክስ.ዲ/25/2004 ተሰርዞ በዚህ መመሪያ ተተክቷል::

## አንቀጽ - 18
## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

16.1 ይህ መመሪያ ከሐምሌ 22 ቀን 1998 ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል::

ተክለወልድ አጥናፉ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ